ዓለም አቀፍ የአማራ ሕብረት (ዓየሕ)

11303 Amherest Avenue, Suite 2

Silver Spring, MD 20902

E-mail: GAC.DCMETRO@gmail.com

ህዝባር፥ቁጥር 8-2012

ግልፅ ደብዳቤ

ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ

አዲስ አበባ

ነሐሴ 8-ቀን 2012 ዓ.ም. August 14, 2020

**ጉዳዩ:- አክራሪ ሙስሊሞችና ፅንፈኛ የኦሮሞ ብሄረተኞች በዉጭ ኃይሎችና በመንግስት መዋቅር በመታገዝ በኦሮሚያ ክልል በአማራዉና በኦርቶዶክስ ክርስቲያን ጉራጌወች፣ኦሮሞወች፣ወላይታወችና ሌሎች ኢትዮጵያዉያን ላይ የፈፀሙትን አረመኒያዊና ዘግናኝ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፉ (Genocide) አጥብቀን እናወግዛለን።**

ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር

ሰኔ 22 ቀን የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ ይህንን ክስተት እንደ ሰበብ በመጠቀም አቅዶና ተዘጋጅቶ ይጠብቅ በነበረ የተደራጀ የአክራሪ ሙስሊሞችና ፅንፈኛ የኦሮሞ ብሄረተኞች ኃይል በየአካባቢዉ ከሚገኘዉ የመንግስት መዋቅር ድጋፍና ቀጥተኛ ተሳትፎ፣ኢንተርኔትን በመዝጋት፣ ” ነፍጠኛ” ብለዉ በፈረጁት አማራዉና ኦርቶዶክስ ክርስቲያያኖችን ኢላማ ያደረገ እጅግ ዘግናኝ የሆነ የዘር ማጥፋት፣ ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ ጭፍጨፉ (Genocide) ከሦስት መቶ በላይ በሚሆኑ ንፁሀን ሰወች ላይ ተፈፅሟል።

ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት በዘር ፍጅቱ ለተሰዉት ሰማዕታት ነፍስ ይማር፣ ከዕልቂቱ ለተረፉትም መፅናናትን ይመኛል።

ይህ ዘርንና ሃይማኖትን ትኩረት አድርጎ የተካሄደዉ ፍጅት የዘግናኝነት ደረጃዉ ሀገረ እግዚአብሄር ተብላ በምትጠራዉ ኢትዮድያ ዉስጥ ተፈፀመ ብሎ ለማመን እጅግ አስቸጋሪ ነዉ። የዘር ማጥፋት ወንጀሉ በተፈፀመባቸዉ ቦታዎች በመሄድ ከጭፍጨፋዉ የተረፉ ሰዎችን አነጋግረዉ ዘገባ ከሰሩ ሚድያዎችና ሊያፅናኑ ሄደዉ ከነበሩ የሃይማኖት አባቶች እንዲሁም ከዕልቂቱ ከተረፉ ተጎጂዎች ድምፅ እንደተረዳነዉ የጭካኔና አረመኔነት ዐይነቱና ደረጃዉ ሂትለር ይሁዴዎችን የፈጀበትን የሆሊኮስት የጋዝ ቻምበር፣ሞሶሎኒ ኢትዮጵያዉያንን በአለም

አቀፍ ህግ በተከለከለ ኬሚካል የመርዝ ጭስ ከፈጀበት፣እንዲሁም ግራዚያኒ ላይ የመግደል ሙከራ መደረግ ተከትሎ በአዲስ አበባ ህዝብ ላይ ካደረሰዉ አረመኒያዊ ጭፍጨፉ እጅግ የከፉና በቃላት ለመግለፅ አዳጋች እንደሆነ ነዉ። ለምሳሌ ያህል የዘጠኝ ወር ነፍሰጡር ከልጆቿና ባለቤቷ ፊት "አማራና ክርስቲያን እንዲወለድ አንፈቅድም በማለት ለአእምሮ በሚከብድ ጭካኔ መሬት ላይ ጥለዉ ሆዷላይ ስለት በማድረግ ባደረሱባት የመግደል ሙከራ ወከባ፣ እንዲሁም የአካልና የአዕምሮ ጥቃት ሆስፒታል ገብታ ሞታለች። እንዲሁም የሰዉን የተለያየ አካላት በመቁረጥ ካሰቃዩ በኋላ ገድለዋል። የሰዉ እጅ ቆርጠዉ እንደ ዱላ በመያዝ ጨፍረዋል። የገደሉትን አካላት በመቆራረጥ ሬሳ መለየት እስከማይቻል ድረስ አድርገዋል። ከጭፍጨፋዉ የተረፉ ወገኖች የተቆራረጠዉን ሬሳ ሰብስበዉ እንዳይቀብሩ በመከልከል ሬሳዉንና ደሙን ዉሻ እንዲልሰዉ ያደረጉ ሲሆን፤አንዳንዱም ሬሳ የጅብ ራት እንዲሆን አድርገዋል። አንዳዶችም በተወለዱበት ቀየ በኦሮሞ መሬት አማራ እንዲሁም ክርስቲያን አይቀበርም ብለዉ ስለከለከሏቸዉ ወደ ሌሎች አጎራባች ቦታወች ተወስደዉ ተቀብረዋል።ከአንድ ቤት አምስት ቤተሰቦች ተቆራርጠዉ የተገደሉበትም አሰቃቂና አሳዛኝ ሁኔታ ሰምተናል። አንድ እናት ሊገድሏት ወደ ቤቷ መምጣታቸዉን ሰምታ ለሺንት ቤት ወደ አስቆፈረችዉ ጉድጓድ በመግባት ለሦስት ቀኖች በዚያዉ ተደብቃ በለቅሶና በሰቆቃ ቆይታ ህይወቷን ልታተርፍ ችላለች።እነዚህን እንደ ምሳሌ ለማሳየት አነሳን እንጅ እየወጡ ያሉ መረጃዎች የሚሳዩት ከዚህ በጣም የከፉ ጭካኔና ግፍ እንደተፈፀመባቸዉ ነዉ። ይህ ሁሉ የተፈፀመዉ መንግስት አለ በሚባልበት አገር ነዉ።

ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት በኦሮሚያ ክልል ዉስጥ በአክራሪ ሙስሊሞችና ፅንፈኛ የኦሮሞ ብሄረተኞች በመንግስት መዋቅር ሙሉ ድጋፍና ተሳትፎ በአማራዉና በኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በሆኑ ጉራጌወች፣ኦሮሞወች፣ወላይታወችና ሌሎች ኢትዮጵያዉያን ላይ የፈፀሙትን አረመኒያዊና ዘግናኝ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ (Genocide) አጥብቀን እናወግዛለን። የደረሰዉ ነገር በጣምም አሳዝኖናል። የመረረ ቁጭት ዉስጥም አስገብቶናል። በዚህ የዘር ማጥፋት ወንጀል የተፈጀዉ አማራዉና ኦርቶዶክሱ ሦስት መቶ ገደማ ነዉ እየተባለ ቢገለፅም ነገር ግን ከዚህ በጣም የበለጠ እንደሚሆን ይታመናል። ከደረሰዉ የዘርና ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ ጭፍጨፋ የተረፉት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት ኢትዮጵያዉያን ወገኖች ቤት ንብረታቸዉ ወድሞ የዕለት ጉርስና ልብስ አጥተዉ በየቤተክርስትያኑ ተጠግተዉ ይገኛሉ። ለሀያና ሰላሳ አመታት ጥረዉ ግረዉ የሰሯቸዉ መኖሪያ ቤቶች፣ ያቋቋሟቸዉ ንግድ ቤቶች፣ሆቴሎች፣እንዲሁም የትዉልድ እዉቀት መገብያ የነበሩ ትምህርት ቤቶች የወደሙባቸዉ ወገኖቻችንን ሀዘንና ዕሮሮ መስማት ልብ ይሰብራል። ቤተሰቦቻቸዉ፣ዘመዶቻቸዉ፣ጓደኞቻቸዉ ወይም ጎረቤቶቻቸዉ ፊታቸዉ ላይ በፍፁም ጭካኔ አካላቸዉ ተቆራርጦ ሲገደሉ ያዩ ህፃናት፣ወጣቶች፣እንዲሁም ማንኛዉም ሰበዐዊ ፍጡር በከፍተኛ የአእምሮ መታወክ ዉስጥ እንደሚገኙ እንረዳለን።

ለሰዉ ልጆች መብት መጠበቅና መከበር የቆመ በአገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገር የሚገኝ ማንኛዉም ሰዉ፣ድርጅት ወይም መንግስት ሊያወግዘዉ ይገባል። እንዲያወግዘዉም ጥሪ እናቀርባለን።

አክራሪ ሙስሊሞችና ፅንፈኛ የኦሮሞ ብሄረተኞች ተደራጅተዉና በመንግስት መዋቅር በመታገዝ በአማራዉና በኦርቶዶክስ ክርስቲያኑ ላይ ይህን የመሰለ ዘግናኝ የሆነ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ የፈፀመት የቻሉትን ያህል ሰዉ ገድለዉ ከጭፍጨፋዉ ያመለጠዉ ሁሉ ፈርቶ ከአካባቢዉ ለቆ እንዲወጣ ለማድረግና ከአማራና ከኦርቶዶክስ ክርስቲያኑ ነፃ የሆነች እስላማዊት ኦሮሚያ የምትባል አዲስ አገር ለመመስረት በማቀድ ነዉ።

ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት ይህንን የተፈፀመዉን የዘር ማጥፋት ወንጀል አስመልክቶ ለኢትዮጵያ መንግስት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቀርባል።

፩. በኦሮሚያ ክልል በአማራዉና ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያዉያን ላይ አክራሪ ሙስሊሞችና ፅንፈኛ የኦሮሞ ብሄረተኞች የፈፀሙት የዘር ማጥፋት ጭፍጨፉ (Genocide) እንጅ ሁከት ወይም ግጭት አለመሆኑን መንግስት እንዲያምንና አሳንሶ ግጭት ዕያለ ከመጥራትም እንዲቆጠብ እንጠይቃለን። ጭፍጨፋዉን ያደራጁትን ኃይሎች ለምን አላማ እንደረጉት መንግስት ለህዝብ ይፉ ማዉጣት ይጠበቅበታል። የአገር ዉስጥም ሆኑ አለም አቀፍ በሰዉ ልጆች መብት መከበር ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች እንዲሁም ሚዲያወች ወደ ቦታዉ ሄደዉ የደረሰዉን እንዲመለከቱ መንግስት ሁኔታወችን ማመቻቸት አለበት።

፪. ይህን የዘር ማጥፋት ዕልቂት ያቀዱት፣የመሩት፣ድጋፍ የሰጡትና የተሳተፉት ሁሉ የመንግስት አካላትን ጨምሮ እዝ ሰንሰለታቸዉን በሚበጣጥስ መልኩ ወደ ህግ እንዲያቀርባቸዉ እንጠይቃለን።

፫. የኦሮሚያ ክልልም ሆነ የፌደራል ብሄራዊ ደህንነት አካላት ይህንን የመሰለ በመቶወች ለሚቆጠሩ ዜጎች ጭፍጨፋ፣ ለሺወች መፈናቀል፣ በቢሊዮኖች ብር ለሚቆጠር ንብረት ዉድመት ያደረሰ ለአገር ደህንነትም ስጋት የሆነ ወንጀል ገና በዕቅድ እንዳለ ተከታትሎ ባለማምከኑ ተጠያቂ መሆን አለባቸዉ። እንዲሁም ጭፍጨፋዉ እየተፈፀመ ባለበት ወቅት ሕዝቡ የድረሱልን ጩኸት ሲያሰማ ኃላፊነታቸዉን ለመወጣት ያልሞከሩት የኦሮሚያ ፓሊስ፣ ልዩ ኃይል፣ በአካባቢዉ የነበረዉ የፌደራል ፓሊስና የመከላከያ ኃይል አመራሮች ተጠያቂ እንዲሆኑ እንጠይቃለን።

፬. በዉጭ አገሮች ሆነዉ የዘር ጭፍጨፋዉ እንዲፈፀም ጥሪ ያደረጉ እንደ ኦሮሞ ሚዲያ ኔት ወርክ ያሉ ሚዲያወች እንዲዘጉ፥እንዲሁም በዚህ ሚዲያ እየቀረቡ ወንጀሉ በስፋት እንዲፈፀም ተከታታይ ቅስቀሳ ያካሄዱ ሁሉ ተጠያቂ እንዲሆኑ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራበት እንጠይቃለን።

፭. በኦሮሚያ ክልል በተለያየ ደረጃ ያሉ የመንግስት አካላት በቀጥታ ተሳትፎም ሆነ ድጋፍ በመስጠት በወንጀሉ ስላሉበት፣እንዲሁም የመከላከል ስራ ባለመስራት ለወንጀሉ ተባባሪነታቸዉን ስላሳዩ መንግስት ተገቢና ከወገንተኝነት የፀዳ ምርመራ ሊያካሂድ ስለማይችል ገለልተኛ የሆነ አጣሪ ኮሚሽን እንዲያቋቁም እንጠቃለን።

እየወጡ ያሉ መረጃወች የሚያማላክቱት ከላይ እስከ ታችኛዉ ዕርከን ያሉ የኦሮሚ መንግስት አመራሮች በወንጀሉ ዉስጥ እንዳሉበት ስለሆነ ሁሉም በጥብቅ መመርመር አለባቸዉ። ይህን ማድረግ የሚችለዉ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን ሲቋቋም ብቻ ነዉ።

ይህ የሚቋቋመዉ አጣሪ ኮሚሽን የሚመረምረዉ በሰኔ ወር የደረሰዉን የዘር ጭፍጨፉ ብቻ ሳይሆን፣በዚሁ አመት በጥቅምት ወር በተመሳሳይ ሁኔታ በኦሮሚያ የተፈፀመዉን ጭፍጨፉ፣የሲዳማ ክልል የመሆን ጥያቄ መልስ አላማኘት ተከትሎ በሀምሌ 2011 የደረሰዉ ዕልቂት፣እንዲሁም በነሀሴ 2010 በጋሞ ተወላጆች ላይ የተደረገዉ ጭፍጨፋን ሁሉ በማካተት እንዲሆን አጥብቀን እንጠይቃለን።

፮. የኦሮሚያ ክልላዊ መንንግስት በሚያስተዳድረዉ ክልል ዉስጥ ለደረሰዉ የዘር ፍጅት፣ንብረት ዉድመት ሙሉ ኃላፊነት በመዉሰድ ቤተሰቦቻቸዉ ለተገደሉባቸዉ የደም ካሳ እንዲሰጥ፣ለቆሰሉና ለተጎዱት ህክምና እንዲያገኙ፣ቤት ንብረታቸዉ ለወደመባቸዉ፣የንግድ ተቋማት ለወደሙባቸዉ የመልሶ ማቋቋም ስራ እንዲጀምር እንጠይቃለን። የፌደራል መንግስቱም ለክልሉ ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲያደርግ እናሳስባለን።

ከዚህ ጋር በማያያዝ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በክልሉ ዉስጥ ይህ ሁሉ ዜጋ ሲታረድ፣የሰዉ ልጅ ደም እንደ ጎርፍ ሲወርድ፣ሺዎች ሲፈናቀሉ፣ያ ሁሉ ቤትና የንግድ ተቋማት ወድሞ ምንም አይነት የሀዘን መግለጫ አለማዉጣቱ ተጎጂዎችንም ባሉበት ቦታ ሄዶ አለማየቱ እጅግ አሳዝኖናል።

ለንፅፅር ያህል ለማሳየት የአርቲስት ሃጫሎን መገደል ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ያደረጋቸዉ የሀዘን መግለጫወችና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ሲታይ በሌላ በኩል ደግሞ ከሦስት መቶ በላይ በፅንፈኞች ለታረዱና ከዕልቂቱ በፈጣሪ ፈቃድ ለተረፉ ተጎጂዎች የሚሳዩት አሳዛኝ ሁኔታን ለመግለፅ ቃላት አይገኝለትም።

ለነገሩማ በዚህ አመት መስከረም ወር አዲስ አበባ በተካሄደዉ የኢሬቻ በአል ላይ የክልሉ ፕሬዘዳንት የሆኑት አቶ ሺመልስ አብዲሳ “ነፍጠኛን በሰበረን ቦታ ላይ ሰብረነዋል” ብለዉ ያደረጉት ንግግር በጥቅምትና በሰኔ 2012 የዘር ጭፍጨፉዉን ለፈፀሙት ኃይሎች ግፊትና ኃይል ሰጥቷቸዋል ማለት ይቻላል። አሁንም ባለፈዉ ሳምንት ዉስጥ ከኦሮሞ ብሮድካስት ኔትወርክ ጋር በአደረጉት ቃለ ምልልስ ያንኑ አባባለቸዉን አጠናክረዉታል። በኮምኒኬሺን ሚኒስተራቸዉ በኩል የተሰጠዉ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ አልተካሄደም ብሎ ወንጀሉን ሺፋን ለመስጠት የተሄደበት መንገድ ይህ ራሱ ወንጀል መሆኑን ማሳወቅ እንፈልጋለን። አቶ ሺመልስ የሚመሯት ኦሮሚያ ለአማራዉና

ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያዉያን የሲፖል ምድር ሆናባቸዋለች። አቶ ሺመልስ አብዲሳ በዚህ መሰል ንግግራቸዉ ለደረሰዉ ወንጀል መሰረት የጣሉ ስለሆነ መጠየቅ አለባቸዉ።

፯. ከዘር ፍጅቱ የተረፉ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች በየቤተክርስቲያኑ ተጠግተዉ ባሉበት ቦታ አሁንም ድረስ እናጠፉችኋለን የሚሉ ዛቻወች እየተደረገባቸዉ መሆኑን በተደጋጋሚ ዕየገለፁ ስለሆነ መንግስት ዋስትና እንዲሰጣቸዉ አጥብቀን እንጠይቃለን።

ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት በክልሉ ፓሊስ፣ልዩ ኃይል፣ወረዳም ሆነ ከተሞች አስተዳደር ዉስጥ ሁሉም የክልሉ ነዋሪ እንዲሳተፍበት ማድረግ ጊዜ የማይሰጠዉ ጉዳይ ነዉ።እንዲሁም ህዝቡ ራሱን መጠበቅ እንዲችል መታጠቅ ለሚችለዉ የግል የተመዘገበ መሳሪያ እንዲኖረዉ መፍቀዱ ተገቢ እርምጃ ነዉ ብለን እናምናለን።

፰. መንግስት በግፍ ለተጨፈጨፉት ሰማዕታት ቢዘገይም ብሄራዊ የሀዘን ቀን እንዲያዉጅላቸዉ እንጠይቃለን።

፱. የአምባላጌዉ፣የአድዋዉና የሌሎች አዉደ ዉጊያወች የጦር መሪ አርበኛ፣ጎበዝ አስተዳዳሪና ዲፕሎማት የነበሩት በሀረር ከተማ የነበረዉ የራስ መኮነን ሀዉልት በፅንፈኞች መፍረሱ አሳዛኝ ነዉ።ተመልሶ እንዲሰራም እንጠይቃለን።

እዚህ ላይ በሀሰት ትርክት ላይ ተመስርቶ ሆን ተብሎ ህዝብን ከህዝብ ለማጫረስ ታቅዶ የተሰራዉ የአኖሌ የጥላቻ ሀዉልት አሁን ኦሮሚያ ዉስጥ እየተፈፀመ ላለዉ የዘርና ሃይማኖት ተኮር ጭፍጨፋ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስለሚኖረዉ ፈርሶ በምትኩ አንድነትንና የጋራ ተጋድሎን የሚዘክር ሀዉልት እንዲሰራ እናሳስባለን።ይህ በሀሰት ትርክት በኢትዮጵያ ጠል ኃይሎች ተቀነባብሮ የተሰራዉ የአኖሌ ሀዉልት እስካልፈረሰ ድረስ ኢትዮጵያ ሰላም ትሆናለች ብሎ ማሰብ የዋህነት ነዉ።

፲. በዘር ማጥፋት ጭፍጨፋዉ ወንጀል ተሳትፈዋል ብሎ የጠረጠራቸዉን መንግስት በቁጥጥር ስር እያዋለ መሆኑ የሚበረታታ እርምጃ ሲሆን ፤ ነገርግን ከወንጀሉ ጋር ምንም አይነት ንክኪ ፈፅሞ የሌላቸዉን፤ይልቁንስ መንግስትን በሰላማዊ ትግል በአደባባይ ዕየተቹና ዕየሞገቱ፤ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት ጎላ አድርገዉ በማዉጣት ይታገሉ የነበሩትን የባልደራስ ለእዉነተኛ ዲሞክራሲ ፖርቲ መሪ አቶ እስክንድር ነጋና ባልደረቦቹ፣የኢሕአን ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነትና ባልደረባቸዉ፣እንዲሁም የኢዜፓ አመራር የሆኑት አቶ ልደቱ አያሌዉ ወንጀል ፈፅመዉ ሳይሆን የፓለቲካ እንቅስቃሴያቸዉን ለመግታት ታቅዶ፤በተለይም አሁን የደረሰዉን የዘር ማጥፋት ወንጀል በስሙ ሊጠሩ የሚችሉና ለተጎጂወችም ድምፅ በመሆን መንግስት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ሊጎተጉቱና ለዐለም አቀፉም ማህበረሰብ ሊያሳዉቁ የሚችሉ ሲሆኑ የደረሰባቸዉ የፓለቲካ ዕስር ስለሆነ በአስቸኳይ እንዲፈቱ እንጠይቃለን።

፲፩. የአስራት ጋዜጠኞች በሙያቸዉ የተሩዱትን ሀቅ አማራዉ በተለየ ሁኔታ በደል እየደረሰበት ነዉ ፤መንግስትም ሊከላከልለት አልቻለም ብላችሁ ዘግባችኋል፥ይህ ደግሞ ህዝብን ከህዝብ አጋጭቷል በሚል መላዉ ቅጡ በጠፋዉ ዉንጀላ ለዕስር ተዳርገዋል። አማራዉ ተለይቶ መበደሉን የህወሓት ማንፌስቶን፣ሕገ መንግስቱን፣የክልል አወቃቀርን፣በገዛ ርስቱ ላይ በሁሉም ከአማራዉ ክልል ዉጭ ባሉ ክልሎች ዉስጥ እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሆነበትን ሁኔታ ማየቱ በቂ ማስረጃ ነዉ።

እስኪ አማራ ክልል ያገኘዉ መሰረተ ልማት ከሌሎች ክልሎች ጋር ይነፃፀር ፣900 የዳስ ትምህርት ቤት ያለበት እኮ ነዉ፤ በ27 አመቱ የህወሃት የስቃይ ዘመንም ሆነ እስካሁንም ድረስ በአማራዉ ላይ ያልደረሰ ምን ነገር አለ? አማራዉ ከነነፍሱ ገደል ተጥሏል፣ከርስቱ መጤ እየተባለ በገፍ ተፈናቅሏል፣አሁንም ቀጥሏል፤በሀረርና ድሬዳዋ 49/50 እንዲሁም 40/40/20 ተብሎ በሚታወቀዉ አፓርታይዳዊ ፖሊሲ ዋነኛ ተጠቂ ሆኗል፤ 2.5 ሚሊዮን አማራ ጠፋ ተብሎ በፓርላማ ቀርቧል፣ኸረ እንዲያዉም ማስረጃወች እንደሚያሳዩት ከ 5 ሚሊዮን በላይ አማራ እንዲያልቅ መደረጉን ነዉ፣አማራዉ ጥንተ ርስቶቹ ወልቃይት፣ጠገዴ፣ራያ፣ መተከልና ደራ ተወስደዉበት የማንነት ጥያቄቸዉ ሳይመለስላቸዉ እዚህ ደርሰዋል፤አብን የተቋቋመዉ አማራዉ የተለየ በደል ደርሶበታል ብሎ ነዉ፤ ይህ ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት የተቋቋመዉም በዚሁ ምክንያት ነዉ።

የደረሰበት በደል አንገፍግፎት አማራዉ ፋኖን አደራጅቶ ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር በመሆን ባደረገዉ ተጋድሎ ህወሓትን አዉርዶ እርስወን ወደ ስልጣን እንዳወጣወት የሚዘነጉት አይመስለንም።

በጣም የሚያሳዝነዉ አሁንም ለዉጥ መጣ ከተባለ በኀላ የአማራዉ ዕልቂት መቀጠሉ ነዉ። ዋናዉ ጥያቄ ይህ በአማራዉ ላይ የሚደርሰዉ ሰቆቃና ግፍ የሚቆመዉ መቼ ነዉ?

የአስራት ጋዜጠኞች ያለዉን እዉነታ ነዉ ያንፀባረቁት። አማራዉ በጣም ተበድሏል ማለት ደግሞ እንዴት አድርጎ ነዉ ሕዝብን ከሕዝብ ሊያጋጭ የሚችለዉ። በዚህም የተነሳ የአስራት ጋዜጠኞች የህሊና እስረኞች ስለሆኑ በአስቸኳይ እንዲፈቱ እንጠይቃለን።

፲፪. ይህ በአክራሪ ሙስሊሞችና በፅንፈኛ ኦሮሞ ብሄረተኞች በአርሲ፤በባሌ፣በሀረርና በጅማ የሚካሄደዉ የሺብር እንቅስቃሴ ለዜጎች ዕልቂትና ሰላም መደፍረስ ብቻ ሳይሆን ለአገር ደህንነትም በጣም አስጊ ስለሆነ ጥልቅ ምርመራና ጥናት በማካሄድ የአገር ዉስጥም ሆነ የዉጭ የፋይናንስ ምንጩን፣የአይዶሎጅና የመሳሪያ ድጋፋቸዉን የማድረቅ ሰፊ ስራ ከወዲሁ መሰራት እንዳለበት እናሳስባለን። የአክራሪ እስልምናን ትምህርት እያስፋፉ ያሉ የሃይማኖቱ አስተማሪወችን በመለየትና ያስተላለፏቸዉን መልዕክቶች በመመርመር ህግ ተላልፈዉ የተገኙት በህግ እንዲጠየቁ እንጠይቃለን።እንዲሁም በአለም ከታወቁት የሺብር ድርጅቶች ከአልሻባብ፣ አይሰስና አልቃይዳ ጋር ግንኙነት ይኖራቸዉ እንደሆን መመርመር አለበት። ይህ እንቅስቃሴያቸዉ በአጭሩ ካልተቀጨ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለምስራቅ አፍሪካ ብሎም የአለምን ሰላም ወደሚያዉክበት ደረጃ ሊሸጋገር እንደሚችል ከላይ የተጠቀሱትን የሺብር ድርጅቶች የቅርብ ጊዜ ታሪክ ዘወር ብሎ መመርመሩ ተገቢ ነዉ።

እንዲሁም አንዳንድ ምሁራን ነን ባዮች በሚዲያ እየቀረቡ ያስተላለፏቸዉ በህዝብ ላይ የሚያነሳሱ አነጋገሮች መመርመር አለባቸዉ። ለምሳሌ ያህል ዶ/ር ገመቹ መገርሳ በዚህ አመት ኤልቲቪ (LTV) ላይ ቀርበዉ “ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኦሮሞዉን የምታጠምቀዉ ኦሮሞነቱን ለዉጣ አማራ ለማድረግ ነዉ” ያሉት ሀሰት የሆነ፣ ነገር ግን በዉስጡ መርዝ የያዘ ንግግር አሁን በአማራዉና ኦርቶዶክስ ክርስቲያኑ ላይ ለደረሰዉ የዘርና ሃይማኖት ማጥፋት ጭፍጨፋ አስተዋፅኦ አድርጓል ብለን እናምናለን። የፍትኅ አካሉ ይህንና ሌሎች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸዉን ንግግሮቻቸዉን እንዲመረምር እንጠይቃለን ።

ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር

አገራችን ኢትዮጵያ ከፍተኛ በሆነ የህልዉና አደጋ ዉስጥ ትገኛለች።የህልዉና አደጋ ዉስጥ ለመኖሯ መገለጫወች አገራችንና ህዝቧን አንድ አድርገዉ በመያዝ ለዘመናት የዘለቁት ዕሴቶች ከፍተኛ የሆነ አደጋ ዉስጥ ገብተዋል።ለምሳሌ፤

ሀ/ በነገድና በቋንቋ ሳትለያይ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በክርስቶስ መንፈስ አንድ አድርጋ የያዘች ክቡርነትዎ “አገር ናት” ብለዉ በትክክል የገለጿት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ አደጋ ዉስጥ ናት። ካህናትና ምዕመኖቿ ዕየታረዱ ነዉ። ከአምሳ በላይ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዉባታል።

ለ/ ከሌሎች ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቹ ጋር በመሆን ኢትዮጵያን እንደ አገር ያቆማትና ከጠላት ጠብቆ ያቆያት አማራዉ በገዛ ርስቱ ላይ መጤና ሰፋሪ እየተባለ እየተጨፈጨፈና እየተሳደደ ይገኛል።

ሐ/ ለዘመናት አያት ቅድመ አያቶቻችን የተዋደቁላት፣የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ የነፃነት ምልክት የሆነችዉ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ አላማችንን መያዝ ወንጀል ዕየሆነ ነዉ። ለዕስርና ለሞትም ዕየዳረገ ነዉ።

መ/ የሁሉም ኢትዮጵያዉያን መግባቢያ የሆነዉ ከአፍሪካ ብቸኛ የራሱ ፊደል ያለዉ አማርኛ ቋንቋችን በስልት ዕንዲዳከም ዕየተደረገ ነዉ።የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሌለዉ ህዝብ ደግሞ ለጋራ ዕድገት ለመስራትም ሆነ ተባብሮ አገሩን ከጠላት ለመጠበቅ አይቻለዉም።

ሠ/ በጎሳ፣ቋንቋ ወይም ሃይማኖት ሳትለያይ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ አሰባስባ የያዘችዉ የአገራችን ዋና ከተማ አዲስ አበባ የዕኔ ናት በሚል ኃይል በሚወስዳቸዉ ተገቢ ባልሆኑ እርምጃዎች ፈታኝ አደጋ ዉስጥ ትገኛለች።

በእኛ እምነት አገራችን ለገባችበት ምስቅልቅል ሁኔታ ዋነኛ ምክንያቶች፤በህወሓት የተቀረፀዉ ሕገ መንግስት፣ጎሳና ቋንቋን መሰረት አድርጎ የተዋቀረዉ ክልል፣ህወሓት፣ እንዲሁም ተረኝነት ናቸዉ።

ኢትዮጵያ ከዚህ አዙሪት እንድትወጣ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሃሳቦች እናቀርባለን።

1. ህወሓት በህዝብ ላይ የጫነችዉን ሕገ መንግስት ከመጪዉ ምርጫ በፊት በአዲስ ሁሉም ባለድርሻ አካላት መክረዉ በሚያፀድቁት ህገ መንግስት መተካት
2. ለሕዝባችን ሰላም ማጣት፣ለሚሊዮኖች መፈናቀል፣ለዘርና ሃይማኖት ተኮር ጭፍጨፋ ዋነኛ ምንጭ እንዲሁም ለአገር ዕድገት ፀር የሆነዉ የክልል አወቃቀር ፈርሶ በፌደራል ክፍለ ግዛቶች (Provincial Federal System) መለወጥ
3. አዲሱ ህገ መንግስት ዉስጥ በጎሳና በሃይማኖት የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋም በህግ የተከለከለ መሆኑን ማስቀመጥ
4. ኢትዮጵያ ለገባችበት ቅርቃር ዋነኛ ተጠያቂዉ ሺብርተኛዉ ህወሓት ስለሆነ እንደ ፓርቲ በህግ እንዲታገድ፤ወንጀል የፈፀመዉን የበላይ አመራሩን ለፍርድ ማቅረብ
5. በሺወች መስዋዕትነት የመጣዉ ለዉጥ አቅጣጫዉን ሙሉ በሙሉ በመሳት በኦሮሚያ የብልፅግና ፓርቲ የተረኝነት አባዜ ስለተጠለፈ፤ይህ አደገኛና አገር አዉዳሚ አካሄድ በአስቸኳይ መቆም ይኖርበታል። ክቡርነትወ የዚህ የተረኝነት መንፈስ ተጋሪ ካልሆኑ፣አገርን ለማዳን የቀረጡና በሙያ ብቃታቸዉ የተመሰከረላቸዉን ኢትዮያዉያን፣የብልፅግና ፓርቲ አባል ያልሆኑትን ሁሉ ባካተተ መልኩ ካቢኔወን እንደገና ቢያዋቅሩ

6. በኢትዮጵያዉያን መካከል ዕርቅና ሰላም ማካሄድ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ መንግስት ኃላፊነቱን በመዉሰድ እንዲሰራበት እናሳስባለን

ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር

እዉነቱን እንነጋገር ከተባለ ይህን የመሰለ አረመኒያዊ ጭፍጨፋ ተካሂዶ  ህዝብ ሲያልቅ፣ከሰቆቃዉ የተረፈዉ መድረሻ አጥቶ ሲላቀስ፣አሁንም ድረስ እንደገና ዕልቂት ለማድረስ ዕየተዛተብን ነዉ በማለት ጬኸቱን ሲያሰማ፤ካሉበት ድረስ በመሄድ የደረሰዉን በዐይንዉ ለማየት፣ከተጎጂወችም በቀጥታ ለመስማት፣ከተቻለም ለማፅናናት ምነዉ ተሳነወት?

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከሁለት ቀን በፊት ስለደረሰዉ ዕልቂት ሲገልፁ ብሄር ተኮር አልነበረም ያሉት በጣም ያሳዝናል። ገዳዮች እኮ ሳይደብቁ "ነፍጠኛ አማራዉን"፣ "ማተብ ያሰረዉን ኦርቶዶክሱን" በለዉ እያሉ ዕኮ ነዉ የፈጁቸዉ። በዚህም ሆነ ባለፈዉ ጭፍጨፋ በብዛት የተገደለዉ አማራዉ ነዉ:: ኦሮሞዉም ሞቷል ብለዋል፣ አወ ትክክል ነዉ ሞቷል፣ በኦርዶክስነቱ ነዉ ኦሮሞዉ የተገደለዉ።ብሄር ተኮር አልነበረም ሲሉ ምነዉ ሃይማኖት ተኮርም መሆኑን አላነሱም። ከዕልቂቱ የተረፉት የደረሰዉን ሁሉ ተናግረዉታል። የተፈፀመዉ ብሄርንና ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ የዘር ማጥፋት (Genocide) ነዉ። ግጭት ነበር ብሎ ማድበስበስ ፈፅሞ አይቻልም። መሆን ያለበት እዉነቱ በገለልተኛ ወገን እንዲጣራ ማድረግ ነዉ የተሻለዉ መንገድ።

ትምህርት ስለሚሰጥ ለንፅፅር ያህል ፤ ሀምሌ 28 ቀን በቤይሩት ከተማ ከመቶ በላይ ሰወችን የገደለ፣አራት መቶ ያህል ሰወችን ያቆሰለ አሰቃቂ ፍንዳታ መድረሱን ተከትሎ የአገሪቱ መሪ በአስቸኳይ ካቢኔዉን ሰብስቦ የአስራ አምስት ቀን አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣የሦስት ቀን ብሄራዊ ሀዘን አወጀ። እንዲሁም መንግስት ካለዉ የአስቸኳይ ጊዜ በጀት የተወሰነ ገንዘብ ለተጎዱት አፋጣኝ እርዳታ እንዲዉል ወሰነ። ይህን ዐይነት ፈጣንና የተሟላ ምላሽ ነዉ ከአንድ መሪ ሕዝብ የሚጠብቀዉ። በዕኛ አገር የደረሰዉ ከዚህ በጣም የባሰና ጠባሳዉ ለዘመናት በቀላሉ የማይሽር ሀዘን ነዉ። ታዲያ ከክቡርነትዎ ሕዝብ እንዲህ አይነት ፈጣንና ቅን ምላሽ ይጠብቅ ነበር። ቢዘገይም አሁንም

ይጠብቃል። በጣም የሚገርመዉ ግን ቤይሩት ለደረሰዉ አደጋ ለሊባኖስ መንግስትና ህዝብ የሀዘን መግለጫ ሲልኩ ሰዐታት ብቻ ነዉ የወሰደበወት።ይህን ዐይነት ፍጥነት ለሚመሯት አገርና ሕዝብ ያለ ምንም አድሎ እንዲያደረጉት እንመኛለን።

ባለፉት ሁለት አመታት ይህ ዐይነት ተደጋጋሚ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ (Genocide) መፈፀሙ በጣም ግራ የሚያጋባና ሁለንተናዊ የሆነ መልስ የሚሻ አንገብጋቢ ጉዳይ ነዉ።

ለማጠቃለል፣ ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት አገራችን ኢትዮጵያ ከተጋረጠባት ዘርፈ ብዙ የህልዉና አደጋ ለመታደግና ሕዝቧም የቀደመዉ አንድነቱን ጠብቆ እንዲኖር ለማስቻልና ዘላቂ የሆነ አገራዊ ሰላም ለማስፈን እንዲቻል፤ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክና ሙያ ማህበራት፣የሃይማኖት አባቶች፣የወጣትና የሴቶች ማህበራት፣ምሁራን፣የዲያስፐራዉ ተወካዮች እንዲሁም ታዋቂ ሺማግሌወችን ያካተተ ብሄራዊ የመግባባት መድረክ መንግስት እንዲያዘጋጅ ጥሪ እናደርጋለን።

ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ከተደቀነባት የህልዉና አደጋ ቸሩ እግዚሀቤር ይጠብቃት::

በሕዝቧ አንድነትና ወንድማማችነት ታፍራና ተከብራ ለዛላለም ትኑር::

## ዶክተር አምባቸዉ ወሮታው ሊቀ መንበር

ዓለም አቀፍ የአማራ ሕብረት (ዓየሕ)

E-mail: GAC.DCMETRO@gmail.com

ግልባጭ

ለክብርት ፕሬዝዳንት ወይዘሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ

ለኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ደመቀ መኮንን አዲስ አበባ

ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ

ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንት ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ

ለአማራ ክልላዊ መንግሥት ርእስ መስተዳደር አቶ ተመስገን ጥሩነህ<br>ባሕርዳር

በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባስደር አቶ ፍጹም አረጋ<br>ዋሽንግተን ዲሲ

ለሰብአዊ መብት ጉባኤ አቶ ቢኒያም አባተ አዲስ አበባ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ማኅበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ያሬድ ኃይለማርያም<br>ብረሰልስና ጄኔቫ